# እንደ ሽሚዝ የሚቀያየር የፖለቲካ እምነትና አቋም

## ክፍል አራት

(የመጨረሻው)

በሸዋይልማ ኪዳኔ (ጀርመን)

አንድ ፖለቲከኛ የአባላቱንና የደጋፊዎቹን ከዚያም አልፎ የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን ከበሬታና አድናቆት ማግኘት የሚችለው ለፖለቲካ እምነቱ በቆራጥነት ያለማወላወል ሲታገል እንደሆነ መናገሩ መድገም ካልሆነብኝ በስተቀር አዲስ ነገር እንዳልሆነ በሚገባ እገነዘባለሁ። ፖለቲካም ተለዋዋጭ ክስተት እንደመሆኑ የፖለቲካ እምነትም ሊለውጥ እንደሚችልም ጠንቅቆ ይገባኛል።የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን የፖለቲካ እምነታቸውን እንደፈለጉ ለመቀየር የማይቸግራቸው፣ አቋማቸውን በሌላው ላይ ለመጫን የማይፈሩ፣ የፖለቲካ ድርጅትን ዝቅ አድርጎ እንደግል ንብረትነት ለማየት የሚፈልጉ ፖለቲከኞችን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ዓይነቱ ፖለቲከኞች ፖለቲካን ቲያትር ያስመስሉታል። ጥያቄው ፖለቲከኞቻችንን ምን ያህል እናውቃችዋለን የሚል ነው።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይህን ጥያቄ ለመመልስ አንድን ፖለቲከኛ በምሳሌነት እንዲያቀርብ ይገደዳል። አስገራሚ የሆነ የአቋም መለዋውጥ ከሚታይባቸው "በተቃዋሚ የፖለቲካ ጎራ" ውስጥ ከሚገኙ ፖለቲከኞች ውስጥ ከመድኅን ፓርቲ አንጃ በመፍጠር የተገለሉት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በአሁኑ ስዓት በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ተመሳሳይ ችግር ይታይባቸው የነበሩት አቶ ማህሞዳ አህመድ ጋአስ የተባሉ የቀድሞ የአርዱፍ ዋና ጸሐፊ የነበሩ ግለሰብ ድርጅታቸውንና የድርጅቱን ደጋፊዎች ከድተው የወያኔን አገዛዝ እውቅና አግኝተው ተለጣፊ አርዱፍ በመፍጠርና ራሳቸውን የድርጅቱ ሊቀመንበር አድርጎ በመሾም ለአቶ መለስ የይስሙላ ዲሞክራሲ ለሰሩት ውለታ በአገዛዙ ሹመት ተስጥቷቸው የተደላደለ ኑሮ ከጀመሩ ሰንብተዋል ። ከሕዝብና ከአገር በላይ ለግል ዝናና ስልጣን ቅድሚያ የሚሰጡትን ፖለቲከኞች መለየት መቻል ይኖርብናል። እንደ ድሮው ዛሬም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ለፖለቲከኞች ፍላጎት ማስፈፀሚያ መሳሪያ እንዳንሆን የበኩላችንን ማድረግ ይገባናል። ታዋቂ ግለሰብ የተቃዋሚ ፖለቲከኞቻችንን ወይም በግልፅ ቋንቋ የነገው መሪዎቻችንን ከመደገፍም ይሁን ከመተቸት በፊት ማንነታቸውን፣ እምነታቸውንና የዓላማ ፅናታቸውን ማወቁ የመጀመሪያው ተግባራችን ሊሆን ይገባል ባይ ነኝ። አለዚያ ውጤቱ መቆጨት፣ ማዘን በፖለቲካና በፖለቲከኞች ላይ እምነት ማጣት ሲሆን ለእኛ የሚተርፈን ነገር ቢኖር ማብቂያው የማይታወቅ ጭቆና የነገሰበት ሥርዓት ብቻ ይሆናል። እንግዲህ ይህ እንዳይሆን ምን እናድርግ ለሚለው ትልቅ ጥያቄ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ።

## *መድኅን*

ኢዴኃን በተቋቋመ ማግስት አቶ ኃይሉ ሻውል ወደ ዋሽንግተን ብቅ ብለው ነበር። አቶ ኃይሉ ሻውል ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጋር ይገናኙና በመድኅን ውስጥ ስለተፈጠረው ሁኔታ እያነሱ ያወጋሉ። አቶ ኃይሉ ሻውል በፕ/ር ስዩም ገላዬ የሚመራው መድኅን ከእኛ ጋር በህብረቱ ውስጥ እየሰራ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እናንተም በመድኅን ስም እየተንቀሳቀሳችሁ ነው። እንዴት ነው አብሮ መስራቱ አይሻልም ወይ ሲሉ ይጠይቃሉ።ኮ/ል ጎሹ በቀረበላቸው ጥያቄ ይበሽቁና : "…መድኅን ማለት ጎሹ ነው። ጎሹ ማለት ደግሞ መድኅን ነው።" በማለት ይመልሳሉ። ለመሆኑ መድኅን እንዴትና በእነማን ተመሰረተ ?

የደርግ ሥርዓት ለመውደቅ ሲንገዳገድ ባለበት የመጨረሻው ሰዓት ላይ በሚያዚያ ወር 1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ) በመባል ይታወቅ የነበረው የተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት ይመሠረታል። ይህ ቅንጅት በአምስት ድርጅቶች የተመሠረተ ቢሆንም የድርጅት አባል ያልሆኑ በግለሰብ ደረጃ የህብረቱ አባል በመሆን ቅንጅቱን በምክር፣ በሞራል፣ በሃሳብ፣ በቁሳቁስና በገንዘብ ይረዱ የነበሩ ብዙ አገር ወዳድ ምሁራንና አዛውንት ኢትዮጵያዊያኖች የተሰባሰቡበት ነበር። ህብረቱን በግለሰብ ደረጃ በአማካሪነትም ይሁን በገንዘብ ይረዱ ከነበሩት አገር ወዳድ ዜጎችና ምሁራኖች ውስጥ እንደ እነ ኮሞዶር ጣሰው፣ ልጅ ሰይፉ ሚካኤል ዘውዴ፣ ደረጀ ደሬሳና ኮ/ል ጎሹ ወልዴን የመሳሰሉ እውቅ ኢትዮጵያዊያኖች ይገኙበት ነበር። በቅንጅቱ ወሳኝ ስብሰባዎች ላይ እነዚህ በፓርቲ ያልታቀፉ ምሁራንና አገር ወዳድ ዜጎች ድምፅ የመስጠት መብት ስላልነበራቸው ይህ ሁኔታ በአንዳንዶቹ ላይ ቅሬታ በመፍጠሩ አንድ በአንድ ህብረቱን እየለቀቁ መውጣት ጀመሩ። እዚህ ላይ ቅንጅቱ የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ የተለያዩ ስብስቦችንና ግለሰቦችን በአንድ መዋቅር ስር ለማካተት መሞከሩ በአሰራር ላይ ችግር ከመፍጠሩም ባሻገር ለህብረቱ መዳከምና መፍረስ መንስኤ ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ እንደ አንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ቅንጅቱን እየለቀቁ ከወጡት መሃከል እንደ እነ ኮሞዶር ጣሰውና ልጅ ሰይፉ ሚካኤል ዘውዴ የመሳሰሉት ተገናኝተው አዲስ የፖለቲካ ድርጅት የማቋቋም አስፈላጊነትን ሃሳብ አፍልቀውና ሰዎችን አሰባስባው ከግራ ክንፍ ነፃ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ተስማሙ። በየጊዜውም እየተገናኙ ስለሚመሰረተው ፓርቲ ለመነጋገር ስብሰባዎችን ማካሄድ ጀመሩ። በአጭር ጊዜ ውስጥም ብዙ ሰዎችን በስራቸው ማሰባሰብ ቻሉ። በሰባተኛው ስብሰባቸው ላይ ኮሞዶር ጣሰው ኮ/ል ጎሹ ወልዴን ብንጠራው ሊጠቅመን ይችላል ሲሉ ሃሳብ

አቀረቡ። በኮሞዶር ጣሰው የቀረበውም ሃሳብ ተቀባይነት አገኘ። የድርጅቱን ፕሮግራምና ደንቡን በርከት ያሉ ሰዎች ሃሳባቸውን እየጨመቁ በብዙ ድካም ተረዳድተው አዘጋጁት። ከነዚህም ግለሰቦች ውስጥ አንዱ ኮ/ል ጎሹ ሲሆኑ እሳቸውም በሙያቸው የሕግ ባለሙያ በመሆናቸው የፓርቲውን መሰረታዊ ሰነዶች የማራምና የማስተካከሉ ኃላፊነት ተሰጣቸው። ከዚህም በተጨማሪ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በፓርቲው ምስረታ ጉባዔ ላይ የመድኅንን ፕሮግራምና ደንቡን ይዘው እንዲቀርቡ ተደረገ።

የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) በአርሊንግተን ከተማ በቨርጂንያ ስቴት በሚገኘው የክሪስታል ጌትዌይ ማሪየት አዳራሽ ውስጥ ቁጥራቸው ከስድስት መቶ በላይ የሚሆኑ ከአውሮፓና ከሰሜን አሜሪካ የመጡ ኢትዮጵያዊያኖች በተገኙበት መጋቢት 12 እና 13 ቀን 1984 ዓ.ም ባካሄደው የምስረታ ጉባዔ ላይ የፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ ለጉባዔው ተሳታፊዎች ቀርቦ በስፋትና በጥልቀት ውይይት ተካሂዶበት ሠነዶቹም የተሟሉና ለአገሪቱ ችግሮች ተገቢ መልስና መፍትሄ እንደሚሰጡ ታምኖበት መድኅን ተመሰረተ። ለምክር ቤት አባልነት በመቶ ሰማንያ ሶስት ድምፅ (183) አራተኛ ሆነው የተመረጡት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በመማክርት ሸንጎው የመድኅን ሊቀመንበር፣ ልጅ ሰይፉ ሚካኤል ዘውዴ ም/ሊቀመንበር፣ ዶ/ር ፍሰሐጽዮን መንግስቱ ም/ሊቀመንበር እና ዶ/ር ፀሓይ ዓለማየሁ ደግሞ የምክር ቤቱ ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ። ክቡርት አምባሳደር ዮዲት እምሩ ለምክር ቤት አባልነት በመቶ አርባ ድምፅ ተመረጡ። ክቡርት አምባሳደር ዮዲት እምሩ በኢትዮጵያ የመድኅን ተወካይ የነበሩ ሲሆን ድርጅቱንም በሕጋዊ መንገድ በአገር ውስጥ ለማስመዝገብ ተልከው በወያኔ/ኢህአዴግ መራሹ የሽግግር መንግስት እምቢተኝነት የተነሳ ፓርቲውን አገር ውስጥ ለማስገባት የተደረጉ ጥረቶች በሙሉ ሊሳኩ አልቻሉም።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በድርጅቱ ውስጥና ከድርጅቱ ውጭ በሚያሳዩት ባህሪያት ላይ ከፍታኛ የሆነ ክፍተትና ልዩነቶች ይታያሉ። ከድርጅቱ ውጭ ፓርቲውን በመወከል በሚሄዱባቸው ቦታዎች እና በሚያደርጓቸው ንግግሮች አድማጭን የመሳብ ችሎታ ያላቸውና በሕዝብም ዘንድ ተውዳጅ የሆኑ ግለስብ ናቸው። ጥሩ ተናጋሪም ብቻ ሳይሆን ጥሩም አድማጭ ናቸው። በድርጅት ውስጥ ግን አብሮ ለመስራት እጅግ በጣም የሚያስቸግሩ፣ ካልመሰላቸው ለምክር ቤትም ይሁን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ራሳቸውን የማያስገዙ፣ የግል ሀሳባቸውን በሌላው ላይ ለመጫን የማይፈሩና በተለይም በሚያቀርቡት ሃሳብ ላይ ጠንከር ያለ የተቃውሞ ክርክር ሲቀርብ ቶሎ የሚበሽቁና የሚናደዱ ግለሰብ ናቸው። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ሃሳበ ግትርነት የሚያጠቃቸው ምሁራን የሚያቀርቡትን ምክርና ጥናት በአብዛኛው የማይቀበሉ በመሆናቸው ብዙዎች ከእሳቸው ጋር አብሮ መስራት ባለመቻላቸውና አንዳንዶቹም እንዳማይችሉ አስቀድመው መገንዘብ በመቻላቸው ቀስ በቀስ ራሳቸውን ከድርጅቱ እንዲያገሉ ምክንያት በመሆናቸው በውጭ ያላቸው ተውዳጅነትና ዝና ብቻውን መድኅንን ከጉዳት ሊያድነው አልቻለም።

## <u>*መድኅን ስንቱን አጣ*</u>

ትናንት ደርግ ተቃዋሚዋቹን ለማግለልና ለመደምሰስ ሲፈልግ አስቀድሞ አድሃሪ፣ ፀረ-አብዮተኛ፣ አናርኪስት፣ በራዥ ወይም ከላሽ፣ ቦርቧሪ፣ ቀኝ መንገዳኛ፣ ገንጣይ ወይም አስገንጣይ…ወዘተ የሚል ስም እየሰጠ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹ ላይ ምህረት የሌለውን ቀይ ዱላውን ያሳረፈባቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። በዚህ ጨካኝ ተግባሩ አገራችን በሌላት ሀብት አስተምራ ያገኘቻቸውን ምሁራን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንድታጣና የተቀረውም ተሰዶ የግዞት ሕይወት እንዲገፋ በማድረግ አገሪቱን የሰው ድሃ ያደረገ መንግስት ነበር። ዛሬ ደግም የወያኔ/ኢህአዴግ ዘረኛ አገዛዝ ሕዝቡን ከፋፍሎ ለመግዛት ይችል ዘንድ የሚያራምደውን የጎሳ ፖለቲካ መስመር፣የሚያወጣቸውን ዘረኛ ፖሊሲዎች የሚጻረሩ ወይም የመቃወም ዝንባሌ የሚታይባቸውን ዜጎች ልክ እንደ ደርግ ለማስወግድ የሚጠቀምባቸው ደርግ-ኢሠፓ፣ የዘር ማጥፋት ወንጀለኛ፣ ጠባብ፣ ትምክተኛ፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ዴሞክራሲ፣ ፀረ-ልማት ፣አሸባሪ፣ ሽፍታ፣ ዘራፊ፣ ወንበዴ፣ ጉቦኛ ወይም ሙሰኛ … ወዘተ የሚሉ ስሞች እየሰጠ ተቃዋሚዎቹን በተለያየ መንገድ ያስወግዳል። በእርግጥ መንግስታት ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችም በየድርጅቶቻቸው ውስጥ የተለያየ አመለካከት ያላቸውንና የሚቃወሟቸውን አባላት ለማግለል ሲሉ የተለያየ ስም ሲሰጡ ማየቱ የተለመደ ነገር በመሆኑ ላይገርመን ይችላል። ሆኖም ግን ስለ ዴሞክራሲ እየሰበኩና ሕዝብን የስልጣን ባለቤት በማድረግ ለስልጣን እንወዳደራለን በሚሉ ፓርቲዎች ውስጥ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሰራር መታየቱ እምነት ሊያሳጣ እንደሚችል ግልጽ ነው። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጠንከር ያለ ተቃውሞ ሲቀርብባቸው ትላንት የወያኔ/ሻዕቢያ ስርጎ ገብ ዛሬ ደግሞ ኢሕአፓና የኢሕአፓ ሠርጎ ገቦች፣ መንፈሰ ደካሞች እያሉ የተለያዩ ስሞች የሚሰጧቸውን እነደእነ ፕ/ር ስዩም ገላዬንና ፕ/ር እጅጉ ደምሴን የመሳሰሉ የመድኅን አመረር አባላትን ትላንት ምን እየሉ ያሞግሷቸው እንደነበር አብረን እንመልከት።

> *„ … በቅድሚያ የመድኅን ፓርቲን አመራር ከለቀቅሁ በኃላ አመራሩን ከእኔ ተረክበው ለፓርቲው፣ ለሕዝብና እንዲሁም ድግሞ ለአገር ከፍተኛ አገልግሎት ለሰጡት አንደኛ ለፕ/ር እጅጉ ደምሴ እንዲሁም ለፕ/ር ስዩም ገላዬ አድናቆቴንና ምስጋናዬን አቀርባለሁ። …“*

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ
ጁን 17 ቀን 2001 ዓ.ም
ዋሽንግተን ድሲ ከተማ ላይ በተካሄደ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ

የኮ/ል ጎሹ ወልዴን አንደበተ ዕርቱነት የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም። ኮሎኔል ይህን የመናገር ችሎታቸውን በመጠቀም ተቃዋሚዎቻቸውን ለማጣጣል የሚጠቀሙበት ቋንቋና አገላለጽ፣ የሚደረድሯቸው ምክንያቶችና ሰበቦች እንኳን የአጭር ጊዜ ትውስታ ያላቸውን ቀርቶ አልፎ አልፎ ጥሩ አድማጮችንም ሳይቀር  የተሳሳተ አመለካከትና ግንዛቤ የማስጨባጥ ችሎታ አለው። በሌላ በኩል በመድኅን ውስጥ የተፈጠረውን ሁኔታ አስመልክቶ በቅርብ ጊዜ በአሜሪካን ውስጥ በሚገኙ ሬዲዮን ጣቢያዎች ላይ ይሰጥዎቻው የነበሩትን ቃለምልልሶች የተከታተለ ሰው ለሚቀርቡላቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ይሰጥዋቸው የነበሩት መልሶች እርስ በርሱ የሚገጫጩ ሃሳቦች ይበዙበት ስለነበር ብዙውን አድማጭ እኚህን ሰው ምንነካቸው እስከማለት አድርሶት እንደነበር አይዘነጋም።

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ ትልቁ ድክመት ሃሳበ ግትርነትና ካልመሰላቸው ራሳቸውን ለብዙሃን ውሳኔም ቢሆን ያለማስገዛት ችግር ነው። በተለይም በፓርቲው ውስጥ በ1986 ዓ.ም በሊቀመንበሩ በኮ/ል ጎሹ ወልዴና በወቅቱ የመድኅን የምክር ቤት ሊቀመንበር በነበሩት በዶ/ር ፀሓይ አለማየሁ እና በወቅቱ የፓርቲው ም/ሊቀመንበርና የመድኅን የአውሮፓ ቅርንጫፍ ተጠሪ  በነበሩት በዶ/ር ፍሰሓጽዮን መንግስቱ መካከል ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት ሊቀመንበሩ የወሰዱት ኢ-ዴሞክራሲያዊ እርምጃ ድርጅቱን ብዙ አባላት ጥለውት እንዲወጡና አንዳንዶቹንም ራሳቸውን ቀስ በቀስ ከፓርቲው እንዲያርቁ ምክንያት በመሆኑ በመድኅን ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ሊጠገን የማይችል ጉዳት አድርሶበታል።

በመድኅን ውስጥ የተነሳውን አለመግባባት የሚመለከት አጣሪ ኮሚቴ እ.ኤ.አ ከአፕሪል 9-10 ቀን 1994 ዓ.ም በተካሄደው የፓርው ምክር ቤት ተመስርቶ ነበር።ከዚህም በተጨማሪ የመድኅን የአውሮፓ ቅርንጫፍ ከሜይ 13 እስከ 15 ቀን 1994 ዓ.ም ለንደን ከተማ ላይ ባካሄደው የተወካዮች ጉባዔ የሆላንድ፣ የእንግሊዝ፣ የጀርመን፣ የፈረንሳይና የሲዊድን ቅርንጫፎች ተወካዮች በተገኙበት ሊቀመንበሩ ኮ/ል ጎሹ ወልዴንና ም/ሊቀመንበሩንና  የአውሮፓ ተጠሪውን ዶ/ር ፍሰሓጽዮን መንግስቱን ጉባዔው ጋብዞ ፓርቲው ያለበትን ደረጃና ተፈጠሩ የተባሉ ቅራኔዎችን በተመለከተ ከሁለቱም ወገኖች የቀረበለትን ሪፖርት አደመጠ። ጉባዔው በፓርቲው የአመራር አካል ውስጥ ለተፈጠረው ችግር፣ ሕጋዊነትንና የዲሞክራሲን መርህ የተከተለ መፍትሄ ለመስጠት ካልተቻለ፣ ለወደፊቱ በፓርቲው አሰራር ላይ የሚያስከትለው ውድቀት ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል አስገንዝቦ የደረሰባቸውን አጠቃላይ ስምምነቶችን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫው ላይ፣

> *„ … የተነሳውን አለመግባባት ለመፍታት የተሰየመው ኮሚቴ የፓርቲውን ህልውና በሚጠብቅ መልኩ ማናቸውንም መረጃ በማሰባሰብ በትጋት እንዲሰራ ጉባዔው ያሳስባል። … ይህ የሚጠበቀው የምርመራ ውጤት በቀጥታ ከተመረጠው ኮሚቴ ሳይቀርብና ሕጋዊው ምክር ቤት ውሳኔ ሳይሰጥበት፣ ማናቸውም ሌሎች መግለጫዎች በሁለቱም ወገን መቅረብ እንደሌለባቸው ጉባዔው ያስገነዝባል። …“*

*የአስቸኳይ ጉባዔ መግለጫ*
*ሜይ 15 ቀን 1994 ዓ.ም*
*መድኅን የአውሮፓ ቅርንጫፍ*

በፓርቲው ውስጥ በውቅቱ የተፈጠረውን እጅግ አሳሳቢ ችግር ምክር ቤቱ በአጠቃላይም ፓርቲው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍታት መቻል በአባላት፣ በደጋፊዎችና በአጠቃላ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ፓርቲው እምነትንና ተቀባይነትን እንዲያገኝ ያስችለው ዘንድ የችግሩ መፍትሂና መፍትሂውን ለማግኘት የሚከናወኑ ተግባራት በሙሉ የዲሞክራሲን መርህ የተከተሉ እንዲሆኑ አጥብቆ የጠየቀው የመድኅን የአውሮፓ ቅርንጫፍ ሰሚ ጆሮ አጥቶ የምክር ቤቱን ሊቀመንበርና የፓርቲውን ም/ሊቀመንበር ከድርጅቱ መባረራቸውን የሚያበስረው የሊቀመንበሩ መግለጫ ወጣ።

በተለይም ብዙ አባላትን አስበርግጎ ድርጅቱን እንዲርቁ ምክንያት የሆነው ይህ መግለጫ በተለይም የምክር ቤቱን ሊቀመንበር ዶ/ር ፀሓይ አለማየሁን አስመልክቶ በተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው እንደሚከተለው ይነበባል።

> *„ … ይህ ሞራልን የሚነካ አደናቃፊ ተግባር በአንድ አገር ጦር ኃይል ስምሪት ላይ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ አድራጊው በአገር መክዳት (treason) ወንጀል ተከሶ የሚቀጣው ቅጣት መገመት አያዳግትም። … ይህ መጥፎ አድራጎት በማንኛውም አገርና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሥርዓት ውስጥ <u>ለከፍተኛ ቅጣት (ሞት ጭምር)</u> የሚያበቃ የአገር መክዳት ወንጀል ነው። … “*

*ዶ/ር ፀሓይ ዓለማየሁንና ዶ/ር ፍሰሓጽዮን መንግስቱን ከፓርቲው አባልነት ማሰናበት አስመልክቶ ካወጡት መግለጫ የተወሰደ*
ሰኔ 5 ቀን 1986 ዓ.ም

*ሠረዙ የእኔ ነው። እንግዲህ ይህን መግለጫ ያነበበ ሰው ከዶ/ር ፀሓይ ጥፋት ይልቅ ጎላ ብሎ የሚታየው ሞት የሚለው ቃል ነው። በተለይም ይህን ቃል አንድ ሕዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን ከሚጥር ፓርቲ መግለጫ ላይ ማንበብ በእውነቱ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነው። የዶ/ር ፀሓይ ዓለማየሁ መግለጫው ደግሞ የኮ/ል ጎሹ ወልዴን እልኸኝነትና ግትርተኝነት ከፓርቲው የውስጥ ገበናነት አልፎ በአደባባይ ላይ በግልጽ እንዲታይ አድርጎታል። ዶ/ር ፀሓይ ዓለማየሁ ለኮ/ል ጎሹ ወልዴ መግለጫ መልስ በመስጠት ለመድኅን አባላት በሙሉ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጻፈው ደብዳቤያቸው ላይ፣-*

*„ … he also refused to abide by the decision of the council regarding separation of the control and management of the special funds from the operating funds of the party….Colonel Goshu was often very disagreeable with members and leaders of the party. …Ambassador Haile Giorgis, member of the Executive Committee, was very distressed and commented that in his opinion "If colonel Goshu had a security force under his command, he would have gotten me shot today." By December, 1993 colonel Goshu was totally out of control, threatening and accusing of all sorts of charges anyone who disagrees with him. …"*

Dr. Tsehai Alemayehu
Chairman of the Council of Representatives
July 1, 1994

በተጨማሪም ከዚህ የዶ/ር ፀሓይ ዓለማየሁ ደብዳቤ ላይ የምንረዳው ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ራሳቸውን ለፓርቲው ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ካለማስገዛት ባሻገር በአንዳንድ የአመራር አባላት ዘንድ ይፈሩም ጭምር እንደነበር ነው። ከዚያ መግለጫ በኋላ አንዳንድ ቅርንጫፎች መግለጫዎችን በማውጣት ቅር የተሰኙበትንና ያልተሰማሙበትን ጉዳዮች እየጠቀሱ ራሳቸውን ከድርጅቱ ሲያገሉ ሌሎቹ ደግሞ ጽምፃቸውን ሳያሰሙ ራሳቸውን ከፓርቲው አራቁ ። በሁለተኛው የመድኅን ጉባዔ ላይ ተካፍሎ በተመለሰው የመድኅን የሲዊድን ቅርንጫፍ ተጠሪ ተዘጋጅቶ ለአባላት በተበተነው ሪፖርቱ ላይ፣

*" … ከእንግዲህ መድኅን ለሊቀመንበሩ የግል ንብረታቸው፣ አባላቱም የግል ተላላኪዎች፣ ለቀመንበሩን ላለማስቀየም መስራት፣ ደሞወዝ መክፈል፣ ቤት ኪራይ መገበር፣ ስልክ እየደወሉ እጅ መንሳት የአባልነት መለኪያው ነው። ከዚህ ውጭ ያለው ፀረ ጎሹነት ነው። … ጉባዔው ትልቅ እድል አምልጦታል። በፓርቲው ውስጥ በመቆየት ሊያገለግሉ የሚችሉ፣ ለአገራቸው የሚሰሩትን ሁሉ ሓሳባቸውን ለማደመጥ ትዕግስት አለማሳየቱ የሊቀመንበሩ clique ዘመቻ ውጤት ለመሆኑ በገሃድ ታይቷል። …"*

ከመድኅን የሲዊድን ቅርንጫፍ
ተወካይ ሁለተኛውን ጉባዔ አስመልክቶ ከቀረበ ዘገባ የተወሰደ
ጁላይ 12 ቀን 1994 ዓ.ም

እንደዚሁም መድኅን የጀርመን ቅርንጫፍ ሊቀመንበርና የቅርንጫፉ መስራች የነበሩትም በተፈጠረው ሁኔታ ባለመደሰት ቅር የተሰኙ መሆኑን ገልፀው የስንብት ደብደቤ ጽፈው ራሳቸውን ከድርጅቱ አገለሉ። በደብዳቤያቸው ላይም በተለይም ጠንካራ ተቃውሞ የሚያቀርቡ አባላትን ለማግለል ሲባል ብቻ የተለያዩ ስሞችን እየለጠፉ ማግለሉን በመቃወም ሲገልጹ፣

*" … በመሰረቱ በአንድ ድርጅት ውስጥ የተለያዩ ሃሳቦች መከሰታቸውና በአመራሩና በአባላቱ ዘንድ መንሸራሸራቸው ለድርጅቱ ጤናማነት አስታማማኝ መሰረቶች ናቸው። በመድኅን ውስጥ ግን አመራሩ ለመስማት የሚፈልገውን ብቻ እንጂ ለየት ያሉ ሃሳቦችን የሚያቀርብ ግለሰብ የመድኅን ሳይሆን የሌላ ድርጅት ጥቅም አራማጅ፣ አፈንጋጭ…ወዘተ እየተባሉ መታማታቸው …"*

ለኮ/ል ጎሹ ወልዴ
ከመድኅን የጀርመን ቅርንጫፍ
ሊቀመንበር ከአቶ ሳምሶን ጌታሁን ከተፃፈ የስንብት ደብዳቤ የተወሰደ
ኦክቶበር 09 ቀን 1994 ዓ.ም

እንደገና ዛሬ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በመድኅን ውስጥ አንጃ እንዲፈጠር በማድረግና ራሳቸውን የቡድኑ መሪ አድርጎ በመሾም የቀድሞ ድርጅታቸው ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ጉዳት ማድረስ ችለዋል።

**አንጃው እንዴት ተፈጠረ?** ጥቅምት 9 ቀን 1995 ዓ.ም በዋሽንግተ ዲሲ ከተማ ውስጥ በተካሄደው የመድኅን ስድስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ፈጽሞ አጀንዳ ባልተያዘበት ጉዳይ ላይ የፓርቲውን የትግል ስልት አስመልክቶ ከቤታቸው በራሳቸው የእጅ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ በፎቶ ኮፒ የተባዛ ባለ ሁለት ገጽ ሠነድ በጉባዔው መሃል ላይ ተነስተው ለጉባዔው ተሳታፊ ማደል ጀመሩ። የሠነዱ ርዕስ :" የኢትዮጵያ መድኅን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) ጠቅላላ ጉባዔ ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ" ይላል። ሠነዱ :" ጥቅምት 9 ቀን 1995 ዓ.ም ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባውን ያካሄደው የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) ጠቅላላ ጉባዔ በፓርቲው ሊቀመንበር በዶ/ር ስዩም ገላዬ የቀረበለትን ድርጅታዊና የፖለቲካ ሪፖርት አድምጦ አጠቃላይ ውይይት በማካሄድ ሁለት ውሳኔውችን አሳልፏል" ይላል። ውሳኔ ቁጥር አንድ ላይ መድኅን በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 9.4 ላይ የሰፈረው መሻሻሉንና በተራ ቀጥር ሁለት ላይ ደግሞ የድርጅቱን ተቋም ወደ ኢትዮጵያ እንዲያስገባ የጠቅላላ ጉባዔ ስድስተኛ መደበኛ ስብሰባ ውስኗል ብሎ ይደመደማል። ጉባዔው ፈጽሞ በአጀንዳ እንኳን ያልያዘው ነጥብ ቢሆንም በቂ ጊዜ ወስዶ ውይይት ይካሄድበታል። የሚቃወሙም ጉዳዩን አስቀድመው በሚስጥር የሚያውቅትም እንደ እነ ዶ/ር ሞገስ ገ/ማሪያም እና አቶ ቸሩ ተረፈም እየደገፉ አስተያየት ይሰጥበታል። በመጨረሻም ጉባዔው በፕ/ር አቻምየለህ ደበላ የሚመራ አምስት አባሎች ያሉበት የጥናት ኮሚሽን መርጦ ያቋቁማል። መድኅን ጠቅላላ ጉባዔውን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫው ላይ፦

*„ … ቀጣዩን የትግል ስልት አቅጣጫ በሚመለከት በስፋት፣በጥልቀትና በዝርዝር ተወያይቷል። … ይህንንም የሚያስፈጽም አምስት አባላት ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ቢበዛ በአንድ ዓመት ውስጥ ጥናቱን አጠናቆ ውጤቱን ለጠቅላላው ጉባዔ እንዲያቀርብ ተወስኖ የኮሚቴው አባላት ተመርጠዋል። … በድርጅቱ ደንብ መሠረት በዕለቱ ፓርቲውን ለሚቀጥለው ሁለት ዓመታት የሚመሩትን የድርጅቱን ሊቀመናብርትና ሌሎች የሥራ አስፈጻሚ አባላትን መርጧል። … በዚህም መሠረት ዶ/ር ስዩም ገላዬን ለሁለተኛ የአመራር ዘመን በድጋሚ በሊቀመንበርነት እንዲመሩ የመረጠ ሲሆን ሁለት ምክትል ሊቀመናብርት ከጀርመንና ከኒውዮርክ ቅርንጫፎች መርጧል። …“*

*መድኅን*
*ጋዜጣዊ መግለጫ*
ኦክቶበር 30 ቀን 2002 ዓ.ም

እንግዲህ ችግሩ የሚጀምረው በዕለቱ በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የቀረበውን ሠነድ ጉባሄው ባለማጽደቁ ነው። በአጭሩ እኔ ያልኩት ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ እንደማለት ነው። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከዚያን ቀን ጀምሮ እንደ እነ ዶ/ር ሞገስ ገ/ማሪያም እና አቶ ቸሩ ተረፈ ከመሳሰሉት ግብረአበሮቻቸው ጋር በመሆን አንድንድ አባላትንና አባላት ያልሆኑ ግለሰቦችን በሚስጥር ማሰባሰብ ጀመሩ። በየካቲት 12 ቀን 1995 ዓ.ም (ፌብሯሪ 8 ቀን 2003 ዓ.ም) በሚስጥር ቨርጂኒያ ውስጥ ስብሰባ በማካሄድና መግለጫ በማውጣት በሕዝብ ዘንድ ሕጋዊ እውቅና ለማግኘት እንዲረዳ በማሰብ የመድኅን ስድስተኛ „ቀጣይ“ ጠቅላላ መደበኛ ጉባዔ በሚያዚያ 11 ቀን 1995 ዓ.ም (አፕሪል 19 ቀን 2003 ዓ.ም) እንዳሚካሂድ አሳውቀው በሚያዚያ ወር ጉባዔው ተካሂዶ ኮ/ል ጎሹ ወልዴም ፕሬዚዳንት ተብለው መመረጣቸውን አሳወቁ። የቨርጂኒያው ሚስጥራዊ ስብሰባ የፓርቲው ደንብና ሕግ ከሚያዘው ውጭ የተካሄድ በመሆኑ የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መድኅን) በየካቲት 19 ቀን 1995 ዓ.ም ኮ/ል ጎሹ ወልዴንና ግብረአበሮቻቸውን ፓርቲው ማሰናበቱን ጋዜጣዊ መግለጫ በማውጣት ለሕዝብ ይፋ አደረገ። አንጃውም ከሚያዚያ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ጅምሮ በይፋ በመንቀሳቀስ በየካቲት 16 ቀን 1996 ዓ.ም የወያኔ አገዛዝ ዕውቅና አገኘ። ፕሬዚዳንቱና ድርጅታቸው ተለያይተው እሳቸው ዋሽንግተ ዲሲ ድርጅታቸው አዲስ አበባ ላይ ሆነው ፖለቲካው በውክልና እየተሰራ ነው፡፤

## የፖለቲካ ታክቲክ

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች በኩል እየታየ ያለው ፈጣን የሆነ ለውጥ የሚያበረታታና የሚደገፍ ነው። የተቃዋሚ ኃይሎች ህበረት ፈጥረው በአንድነት ተባብረው መስራት አለመቻላቸው ሲያሳዝነንና ሲያስቆጨን እንዳልነበር ዛሬ ባልጠባቅነው ፍጥነት ከህብረት አልፎ መዋሃድና ለመዋሃድ ስምምነት መፈራረም ዓይናችን ወይም(እና) ጆሮአችን የለመደው የፖለቲካ ዜና ከሆነ ሰንብቷል። ኢዴፓ ከኢድኃፓ (ኢዲዩ)በመባል ከሚታወቀው ድርጅት ጋር በመዋሃድ ኢዴአፓን መፍጠር መቻሉ አስደሳች ዜና ነበር። በእርግጥ ኢዴአፓ የሶስት ድርጅቶች ( ኢዴፓ፣ኢህዴግና ኢዲዩ) ውጤት መሆኑን ብዙ ሰው ልብ ብሎ የሚያውቀውው ጉዳይ አይመስለኝም። እኔ በግሌ የድርጅቶችን መዋሃድ በመርህ ደረጃ የምደግፈው ቢሆንም ከውህደት በፊት የተቃዋሚ ድርጅቶች እንከን የሌለው እውነተኛ ህብረት ፈጥረው በአንድነት ተባብረው የመስራት ችሎታ፣ ልምድና ባህል ካዳበሩ በኋላ ተመሳሳይ ዓላማና ግብ ያላቸውና አንድ ዓይነት ራዕይ አለን ብለው የሚያምኑ ድርጅቶች የበለጠ በመቀራረብ ቀስ በቀስ እያደገ ወደ ውህደት የሚያመጣ ስምምነት ደርሰው አብረው ቢሰሩ የአባላቶቻቸውና የደጋፊዎቻቸውን ከዚያም አልፎ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ሊኖረው የሚችል ውህደት መፍጠር ይችላሉ የሚል የፀና እምነት አለኝ። እኔ በግሌ የአዝጋሚ ወይም የጥጋናዊ ለውጥ ደጋፊ እንጂ የስር ነቀል ለውጥ ደጋፊ አይደለሁም። እኛ ያለመታደል ሆኖ ዛሬ እንደ አውሮፓዊያኖቹ አብሮ የመብላትና አብሮ ፖለቲካን (በህብረት) የመስራት እድገት ላይ ደርሰናል ማለት ይከብደኛል። ዛሬ እኛ ያለነው ገና አብሮ መብላቱ ላይ ነው። የነገን ባላውቅም። ስለሆነም ሕዝቡ ሰልችቶት ወይ ተባበሩ አሊያም ተሰባበሩ ስላለ ይመስላል „ውህደት“ በእኛ አገር የፖለቲከ ፋሽን ሆኗል።

ዛሬ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በሚፈጠሩ ውህደቶች ላይ ሶስት መሠረታዊ የሆኑ ችግሮች ይታዩኛል። የመጀመሪያው ውህደቱ ከሁሉም በላይ የሚያተኩረው የሕዝብን ድጋፍ ለማግኘት ወይም ከሕዝብ ተቃውሞ ለማምለጥ ሲባል ብቻ የሚደረግ የፖለቲካ ታክቲክ መሆኑ ነው። ሁለተኛው ውህደቱ ከውህደቱ በፊት ውህደቱን የፈጠሩት ድርጅቶች ከነበራቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴ፣ ጥንካሬና የሕዝብ ድጋፍ በተሻለ መልኩ ጠንክረው ሲንቀሳቀሱ ማየት አለመቻላችን በራሱ ችግር መኖሩን ይነግረናል። ሶስተኛው ውህድቱ ለአቶ መለስ አገዛዝ የተመቻቸ ዒላማ ስለሆነለት በተዘዋዋሪ መንገድ ወያኔ ውህደት እንዲፈጠር ሲያበረታታ እናገኘዋለን። እነዚህን የግል እምነቶቼን ተራ በተራ ለማስረዳት ልሞክር።

በመጀመሪያ የሕዝብ ድጋፍን ብቻ ለማግኘት ሲባል ብቻ የተደረገውን ውህደት እንመልከት። የኢዴፓና የኢዲዩ ውህደት እስከ ዛሬ ድረስ ተቃውሞና ችግር ሊገጥመው የቻለው እንደ ኢዲዩ አባላት አባባል ከሆነ ውህደቱ ሲፈጠር አባላቱ ተመካክረውበትና የሁሉንም ድጋፍ አግኝቶ ሳይሆን እንዲያው በዘፈቀድ በድርጅቱ መሪዎች ቀና አመለካከትና ፍላጎት ላይ ብቻ ተመስርቶ የተፈጠረ ውህደት በመሆኑ ውህደቱን በመርህ ደረጃ ሳይሆን ከአባላትና ከደጋፊዎች እውቅና ውጭ የተፈፀመ በመሆኑ ብቻ ነው። የጦማር ጋዜጣ ውህደቱ የገጠመውን ተቃውሞ አስመልክቶ ሲዘግብ፦

> *„ ... የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ፓርቲ ወይም ኢዲዩ ተብሎ የሚጠራው ፓርቲ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) ጋር የፈፀመው ውህደት የግለሰቦች እንጂ የፓርቲዎች አይደለም ሲሉ የኢዲዩ አባላት የሆኑና ውህደቱን የሚቃወሙ ሰዎች ለጋዜጣው ገልጸዋል። ...“*

ጦማር
ጳጉሜን 4 ቀን 1995 ዓ.ም

እንግዲህ በአንድ በኩል በራስ መንገሻ ስዩም የሚመራው የኢድዩ አመራር ከኢዴፓ ጋር ተዋህዶ ኢዴአፓን ሲፈጥር በቀና አመለካከት የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ያስችላል ከሚል ቀና አመላካከት በመነሳት ሊሆን ይችላል፡ በሌላ በኩል ኢዴአፓን የፈጠረው የኢዲዩ አመራርና በኢዴአፓ ውስጥ ያለውን ኢዲዩን በተመለከተ የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ፈቃድና ድጋፍ ያልታከለበት በመሆኑ አባላቱ የሚመለከቱት እንደ አንድ ከኢዲዩ የተገነጠለ ቡድን ወይም አንጃ አድርገው በመሆኑ እነሱ እኛን በፍጹም አይወክሉም ባዮች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ኢዴአፓ በተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃኅ) ውስጥ ከኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት ተሓድሶ ወይም በአጭሩ ኢዲዩ ተብሎ ከሚታወቀው ድርጅት ጋር አብሮ እየሰራ ነው። እንግዲህ ኢዴፓ ከኢዲዩም ከኢዲዩም አንጃ ጋር አብሮ እየሰራ ነው ማለት ነው። ታዲያ ሕዝቡ ለየትኛው ኢዲዩ ድጋፉን ይስጥ ?!

ሌላው ዛሬ ከሕዝብ ተቃውሞ ለማምለጥና ማንኛውንም ዓይነት ጥርጣሬ ከራስ ላይ ለማንሳት ሲባል ብቻ ወደ ውህደት ለማምራት የሚያስችል ስምምነትን የሚመለከት ጉዳይ ይሆናል። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) አባል ድርጅቶች በሆኑት በመኢአድና በኢዴአፓ መሃከል ሊፈጠር የነበረው ውህደት በመኢአድ ፕሬዚዳንት በታህሳስ 8 ቀን 1996 ዓ.ም በእጅ በተፃፈ ደብዳቤ ሞቶ የተቀበረ በመሆኑ እንለፈው። ሌላው እንደገና ኢዴአፓ በፕ/ር ስዩም ገላዬ የሚመራውን መድኅንን ጨምሮ ከ14 የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን በሓምሌ 26ቀን 1995 ዓ.ም ኢዴኃኅን በመሰረት በሶስተኛው ቀን ማለትም በሓምሌ 29 ቀን 1995 ዓ.ም ዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ውስጥ የኢዴአፓ ሊቀመንበር ክቡር ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ ከመድኅን አንጃ መሪ ከሆኑት ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጋር በመሆን ወደ ውህደት ለማምራት የሚያስችል ስምምነት ተፈራረሙ። እዚህ ላይ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ግልጽነት የጎደለውን ፖለቲካቸውን ከሕዝብ ጥርጣሬ ለማራቅ የነበራቸው ብቸኛ አማራጭ ይህ መንገድ ብቻ በመሆኑ በስምምነቱ የፖለቲካ ትርፍ አግኝተውበታል ማለት ይቻላል። በጊዜው የኢዴአፓ ሁኔታ ያላስገረመው ሰው አልነበረም። የግሉ ፕሬስ የተደረገውን ስምምነት አስመልክቶ ሲዘግብ፣

> *„ ... በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃኅ) ውስጥ የዋና ፀሓፊነት ኃላፊነት ያገኙት ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ ኅብረቱን በመሰረተው ሁሉን አቀፍ የፓርቲዎች ጉባዔ ላይ ባለመሳተፋቸውና እንዲሳተፉ ባለመደረጋቸው በአሜሪካ ውስጥ ባሉ የሬዲዮ ጣቢያዎች አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ሲያካሂዱ ከነበሩት በኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከሚመራው የመድኅን ፓርቲ ጋር ለመዋሃድ መስማማታቸው በብዙዎች ተመልካቾች ዘንድ ትዝብትና ገረሜታን አሳድሯል። ...“*

ማትሚኖ
ነሓሴ 2 ቀን 1995 ዓ.ም

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ስምምነት ከሰማይ የወረደ ሲሳይ እስኪመስል ድረስ በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የኮ/ል ጎሹ ወልዴ የንግግር መክፈቻና መዝጊያ በመሆን መሣሪያ ሆኗል ብል ማጋነን አይሆንብኝም። በሌላ በኩል ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ወደ አገር ቤት የመድኅን ፕሬዚዳንት ተብለው ከመግባታቸው በፊት የግድ ከኢዴአፓ ጋር ወህደቱን እንዲፈጥሩ የሚያስገድዷቸው ሁኔታዎች አሉ። ስለሆነም እሳቸው ዋሽንግተን ዲሲ ከተማ ላይ ሆነው እሳቸው ባልተገኙበት ውህደቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተፈጠረ የሚለው የነገው ዜና ፈጽሞ ሊገርማን አይግባም። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የመድኅንን አመራር ለፕ/ር እጅጉ ድምሴ ካስረከቡ በኋላ በድርጅቱ ውስጣ አንጃ ተፈጥሮ የአንጃው መሪ ሆነው ወደ ፖለቲካው መድረክ እስከተመለሱበት ጊዜ ድረስ እብዛኛውን ጊዜያቸውን በኃይማኖቱ ላይ ያሳልፉ ስለነበር በኃይማኖቱና በፖለቲካው እንቅስቃሴያቸው መሃከል ያለው ልዩነት ለተመለከተና በተለይም ድርጅታቸውን ለማስመዝገብ የሚያስፈልገውን ፊርማ አሰባስበው ያገኙት ከዚሁ የእሳቸውን እምነት ተከታይ ከሆኑ ወገኖቻችን መሆኑ በራሱ ወደ አገር ቤትም ቢመለሱም ከፖለቲካው ይልቅ ፊታቸውን ወደ ኃይማኖቱ በመለስ ፖለቲካውን እንደ አባልነት የሚቀጥሉበት ጉዳይ ይሆናል የሚል ድምዳሜ ላይ ሊያደርሰን ይችላል። ስለሆነም መድኅንን ወደ አገር ቤት መግቢያ የፖለቲካ ጆከርና ውህደቱን ደግሞ የፖለቲካ ስምን ለመጠበቅ በመሳሪያነት እንዲያገለግል ይረዳ ዘንድ እየተጠቀሙበት ነው። በእርግጥ በመድኅንና በኢዴፓ መሃከል የፕሮግራምና የዓላማ ተመሳሳይነት መኖሩን የሁለቱን ድርጅቶች ፕሮግራም የተመለከት በቀላሉ ሊገነዘበው የሚችል ጉዳይ ነው።የመድኅንን ፕሮግራም ለተመለከት ከመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) ተገንጥለው የወጡት እንደ እነ አቶ ልደቱ አያሌው ያሉ ወጣቶች ፕርግራም ለመንደፈና የድርጅት ስም ለማውጣት ጊዜ የፈጃባቸውም አይመስለኝም። የኢትዮጵያ መድኅን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲን ፕሮግራም እንዳለ በማስቀመጥ መድኅን የሚለውን ቃል ብቻ በማውጣት ኢዴፓን የመሰረቱ ይመስለኛል። ይህን ስል ያለ ምክንያትም አይደለም። ስለ ኢዴፓ አመሰራረት በመጠኑም ቢሆን የማውቀው ጉዳይ ስላለኝ ነው። አንድ ሊገባኝ ያልቻለ ነገር ቢኖር ኢዴፓ ከመድኅንና ከኢዲዩ ጋር ብቻ ሳይሆን ከነዚሁ ሁለት ድርጅቶች ውስጥ ተገንጥልው ከወጡ አንጃውቻቸው ጋር አብሮ በመስራት የሚያገኘው የፖለቲካ ፋይዳ ምንድነው ? ለእኔ ግን እንደ አንድ መጥፎ የፖለቲካ ባህል ሆኖ ይታየኛል። እንግዲህ ኢዴፓን በውህደት ስም የአንጃዋች መሰብሰቢያ እንዲሆን የራሱ የድርጅቱ አፈጣጠርና ባህሪው ያስገድደው

ይሆን ? አላውቅም። አንድ ነገር ግን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን። መዐሕድ ባይኖር ኖሮ ኢዴፓም መኢአድም የሚባሉ ድርጅቶች ዛሬ ሊኖሩ አይችሉም ነበር። እንግዲህ ተመልከቱ የውህደት ስምምነቱ እንኳን አንጃዎችን መሰረታቸው አንድ የነበረውን የመዐሕድ ፍጥረት (ውጤት) ኢዴፓንና መኢአድን አቀራርቦ ወደ ውህደት ማምጣት እንኳን አልቻለም። ዛሬ ደግሞ ይባስ ብሎ ኢዴአፓ መስርተው የነበሩት ኢዴፓና ኢዲዩ መለያየታቸውን እየሰማን ነው።

ሁለተኛው ኢዴአፓን የፈጠሩት ድርጅቶች ከውህደቱ በፊት ከነበራቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ይበልጥ ሊያሰራ የሚችል ጥንካሬና ጉልበት አግኝተው ከሌሎቹ ጋር ህብረት ፈጥረው ሕዝቡን በማንቀሳቀስ ለአገዛዙ የማይመቹ ጠንካራ ኃይል ይሆንሉ ብልን ስንጠበቅ እያየነው ያለነው ግን የጠበቅነውን አይደለም። እንደ እኔ ላለ በዘር ፖለቲካ ፈጽሞ ለማያምን ኢትዮጵያዊ ከዘረኛው ወያኔ በስተቀር ፈጽሞ ሌላ ድርጅት ዝር በማይልባት የትግራይ ክፍለ ሀገር ውስጥ ኢዲዩን የመሰለ ሕብረብሄር የፖለቲካ ድርጅት ማግኘት ቀላል አልነበረም። ኢዲዩ አብዛኛው ደጋፊዎቹ በትግራይ ውስጥ ስለሚገኙ ወያኔ ከማንም ይበልጥ ይፈራው ስለነበር በኢዲዩ አባላት ላይ ትላንት ይደርስ የነበረው የእስራት፣ ከመኖሪያ የመፈናቀል፣ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች የመታገድና ሕገወጥ ግድያ እና ከዚያም አልፎ ገና ለገና እገሌ የኢዲዩ ወይም የራስ መንገሻ ስዩም ደጋፊ ነው እየተባለ ፍዳውን ያይ የነበረው የኢዲዩ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ይፋፀሙ የነበሩ በደሎች እስክ ቅርብ ጊዜ ድረስ የምንሰማው ዜና እንደነበር ሁላችንም የምናስታውሰው ይመስልስኛል። ከውህደቱ በኋላ ግን የኢዲዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከትግራይ ጓዙን ጠቅልሎ የህብረቱ ጽ/ቤት ወደ ሆነችው አዲስ አበባ የገባ እስኪመስል ድረስ የኢዴአፓ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በትግራይ ውስጥ የሚሰማ አይደለም። እዚህ ላይ ውህደቱ እኛ ሳናውቀው የተፈፀመ ነው ብለው የተቃወሙትን አባልት ግምት ውስጥ ካስገባን በትግራይ ውስጥ የኢዲዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መድከም ምን እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን። እንግዲህ በዚህ ውህደት ማን አተረፈ ማን ከሰረ የሚለውን ጥያቄ መልሱን ለአንባቢያን መተው እመርጣለሁ።

ሶስተኛው ውህደቱ ለአቶ መለስ አገዛዝ በዒላማነት የተመቻቸ እስኪመስል ድረስ የወያኔ አስተዳደር ከውህደቱ አባል ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች ይበልጥ ለውህደቱ የተቆርቋሪነት ስሜት ማሳየቱ በራሱ ጤነኛ ምልክት አይደለም። ውህደቱን በሚመለከት የኢዲዩ አባላት ተቃውሞ ሰሚ ጆሮ አጥቶ የሁለቱን ፓርቲዎች ውህድት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ወይም የአቶ መለስ አገዛዝ ውህደቱን መደገፉንና ማጽደቁን መስከረም 15 ቀን 1996 ዓ.ም ማስታወቁ አይዘነጋም። የወያኔ አገዛዝ ውህደቱን ለምን ሊደግፈው እንደፈለገ መረዳት የሚያቅተው ሰው ያለ አይመስለኝም። በመጀመሪያ ወያኔ ውህደቱን በመደገፉ ውህደቱን የተቃወሙትን የኢዲዩ አባላትን ከኢዲዩ ጋር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲለያዩ በማድረግ ኢዲዩ ከውህደቱ በፊት የነበረውን ጥንካሬ እንዲያጣ በማድረግ ለህልውናው አስጊ ያልሆነ ደካማ ውህደት እንዲፈጠ አድርጓል። ለወያኔ የደህንነት ኃይልም ሁለት የተቃዋሚ ድርጅቶችን ወይም የየራሳቸው ህልውና ጠብቀው በህብረት የሚሰሩ ድርጅቶችን ከመጠበቅና ከማሳደድ ይልቅ ውህድት ፈጥረው እንደ አንድ ድርጅት የሚንቀሳቀስ ኃይልን ዒላማው ውስጥ ማስገባት እንዳሚቀለው ግልጽ ነው። በአጭሩ በአገራችን ውስጥ እንከን የሌለው ጠንካራ የተቃዋሚ ኃይል ተፈጥሮ ሲንቀሳቀስ ባለየንበት ሁኔታ ለይ እየተገኘን ውህደቱ ከፖለቲካ ታክቲክና መሳሪያነት ውጭ የአገራችንን የፖለቲካ እድገት የጠበቀ ነው ለማለት ያስቸግረኛል። ሆኖም ግን አንዴ ውህደት ተፈጥሯልና ኢዴአፓን ከልብ ከሚደግፉ ዜጎች ውስጥ አንዱ መሆኔን በዚህ አጋጣሚ ሳልገልጽ ማለፍ አልፈልግም።

## የፖለቲካ ባህል ለውጥ አስፈላጊነት

ፖለቲካ የእለት እንጀራችን ላይ ሳይቀር የሚያሳርፈው ተጽዕኖ ቀላል አይደለም።የአንድ አገር ሕዝብ በሙሉ የፖለቲካ ሥራ እንዲሰራም አይጠበቅበትም። ህዝቡ የስልጣን ባለቤት ቢሆንም የፖለቲካ ጫወታውን የሚጫወቱት ፖለቲካኞቹ እንደሆንም ግልጽ ነው። ሆኖም ግን የስልጣን ባለቤት የሆነው ሕዝብ ደግሞ ድምፁንና እምነቱን ሰጥቶ ለስልጣን የሚያበቃውን የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች እና መሪያቸውን ግን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል። ነገ ሕዝቡ የስልጣን ባለቤት ሲሆን የዛሬው የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መሪ የነገው ጠቅላይ ሚኒስትራችን ሊሆን ይችላል። ስለሆነም የዛሬውን የተቃዋሚ ድርጅት መሪ በሚገባ ማንነቱ ሳናውቅ ነገ ለአንድ የምርጫ ዘመን እንኳን ስልጣን ላይ ብናወጣው ከዛሬዎቹ ገዢዎቻችን የተሻለ ለመሆኑ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ የለንም።አንዳንድ ጊዜም የዛሬዎቹን የተቃዋሚ መሪዎቻችንን ለመተቸት የነገው ገዢዎቻችን እስኪሆኑ ድረስ የምንጠብቅም ይመስላል። የዛሬዎቹን ገዢዎች በመርገም ብቻ ነገ ጥሩ አስተዳዳሪዎች ማግኛት አንችልም።

ያለመታደል ሆኖ ኢትዮጵያዊያኖች ይሉኝታ የሚሉት በሽተኛ ባህል የሚያጠቃን በመሆኑ በአብዛኛውን ጊዜ ተቃውሞአችንን የምንገልጸው በዝምታ፣ በመለገም እና በማልመጥ ነው። ይህ ብቻውን በቂ አይደለም። የምንመኛውን ለውጥም ማምጣት አይችልም። የዝምታውን ተቃውሞ በቤተሰብ ደረጃ አስቀርተን የአገርና የወገን ጉዳይ ላይ ድምጻችንን ከፍ አድርገን በየመድረኩና በማሰማት ከዚያም አልፎ በአዳባባይ ላይ ተቃውሟችንን የማሰማት ባህል ማሳየት ስንጀምር የስልጣን ባለቤት ለመሆን ጊዜ አይፈጅብንም። ያ ሳይሆን ግን ማንም እየተነሳ የዝምታ ተቃውሞችንን ለራሱ በሚያመቸው መንገድ በመተርጎምና እንደ ድጋፍ አድርጎ በመውሰድ የፖለቲካ መሳሪያው አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል። በእርግጥ በመጀመሪያ ሕዝቡን አስተባብሮ

የትግል አቅጣጫውን በማሳየት ወደ አደባባይ የሚጠሩን ጠንካራ የተቃዋሚ ድርጅቶችና የሙያ ማህበራት እንዲኖሩን ያስፈልገናል። በተቃዋሚው ድርጅት ውስጥ ብዙ ዶ/ር ታዬዎች እንዲኖሩን ያስፈልገናል። በአንድ በኩል ዛሬ አንዳንዶቹን የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ከስማቸው በስተቀር ማንነታቸውን በሚገባ ጠንቅቀን አናውቅም። ስለሆነም ትላንት ድጋፋችንን ስንሰጣቸው እንዳልነበር ዛሬ ከድተውን የወያኔን አገዛዝ እያገለገሉ ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ቢሳሳቱም አገዛዙን የሚቃወሙ በመሆናቸው ብቻ ገና ልንመክራቸውና ልንተቻቸው ስንል ቀድመው የሚቆጡ ናቸው። ግለሰብ ታዋቂ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎችም ሆኑ ድርጅቶቻቸው ሲሳሳቱ በመምከር፣ በመገሰጽና በመተቸት ስህተተቱን እንዲያርሙ የማደረግና ፈጽሞ አንሰማም ሲሉ ደግሞ ድጋፋችንን በማንሳት ከፖለቲካው የጫወታ ሜዳ በማገለል እንደ ሕዝብ በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ማሳረፍ የምንችለውን ተጽዕኖ በመጠቀም ራሳችንን ከማይጠቅሙ የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰብ መሪዎች  መጠበቅ ካልቻልን ዞሮ ዞሮ የብልሹ ፖለቲካ ሰለባዎች የምንሆነው እኛው እራሳችን መሆናችንን መገንዘብ ይኖርብናል። በመሆኑም የፖለቲካ ባህል ለውጥ ያስፈልገናል።

በእርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የይሉኝታን ሠንሰለት እየሰበሩ የተሳሳቱ የተቃዎሚ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ላይ ጠንከር ያሉና ገንቢ የሆኑ ትችቶችን የሚያቀርቡ ፀሓፊዎችን ትንታንኔ አዘል የሆኑ መጣጥፎችን ማንበብ ጀምረናል። ለምሳሌ በቅርቡ በመኢአድና በኢዴአፓ መሃከል ተሞክሬ የከሸፈውን ውህደት አስመልክቶ አቶ ዐባይ በነበሩ ቀነኒ የተባሉ የአንባቢያቸውን የውስጥ ስሜት በብዕራቸው መኀርኀር የሚችሉ እጅግ በጣም ጥሩ የሆኑ ፀሓፊ በጦቢያ መጽሄት ቁጥር 8 በመጋቢት 1996 ዓ.ም እትሙ ላይ ውህደቱ የከሸፈው በብቃት ማነስና በፖለቲካ ዋልጌነት ነው በሚል ርዕስ ባቀረቡት መጣጥፍ ላይ በእኛ አገር ተቃዋሚን መተቸት ያለበትን ችግር በሚመለከት ሲናገሩ፣

> *„ … ወልደ ማርያም ትክክል ነው፣ ገብረ ማሪያም ግን ተሳስቷል ማለትና ለእውነት መመስከር በእኛ አገር ፖለቲካ ችግር አለበት። በጠላትነትና በወገንተኝነት ያስፈርጃል። በጅምላ ማውገዝ አንተም ተው አንተም ተው የሁለት ፈራጅ መሆን እስከዛሬ ሞክረነው አልጠቀመንም። …“*

በማለት በመኢአድና በኢዴአፓ የተሞከረው ውህደት የከሸፈው በአቶ ኃይሉ ሻውል ምክንያት መሆኑን ባቀረቡት ጹሑፍ ውስጥ ገልፀዋል። በአብዛኛውን ሁኔታውን እንደ አቶ ዐባይ በነበሩ ለተከታተለ ሁሉ ድፍረቱን እንደ እሳቸው አጥቶ እንጂ ፀሓፊውም ባይነግሩን ጥፋተኛውን ሁሉም ያውቀው እንደነበር መገመት አያዳግትም። ፀሓፊው በመጣጥፋቸው ውስጥ ሲጠቃቅሷቸው የነበሩትን ሠነዶች በሙሉ የመመልከት እድሉ ገጥሞኝ ስለነበር ከፀሓፊው ጋር ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ። ይህ ማለት ግን ፀሓፊውንም ወይም የፀሓፊውን ሃሳብ የሚጋሩትን በሙሉ በመኢአድ ተቃዋሚነትና በኢዴአፓ ደጋፊነት ፈጽሞ ሊያስፈርጅ አይገባም።

የተቃዋሚ መሪዎቻችን ስንደግፋቸው እንጂ ስንተቻቸው ስምተውን አያውቁም። ያውም በአደባባይ። በአንባቢዎች ዘንድ እጅግ በጣም ተወዳጅና ዝነኛ የሆኑት ፀሓፊ አቶ ሓሰን ዑመር አብደላ በጦቢያ መጽሔት ቁጥር 9 የሚያዚያ ወር  1996 ዓ.ም እትም ላይ የመቀለድ ወጋችንን ያቀጨጨ ምርር ያለ ምር በሚል መጣጥፋቸው ላይ ስለ ተቃዋሚዎቻችን ሲናገሩ፡-

> *„ … የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን በካርቱንም ሆነ በቀልድ አማካኝነት መተቸት ያልተለመደ ነው።…በባዶ ተኮፍሰው ለራሳቸው እንጂ ለኃላፊነታቸው ቁብ ያልሰጡትን የፖለቲካ አመለከንቱዎች ማጋለጡ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ለነገ የማይባል ተግባር ነው። …“*

ይሉናል። ይህ የአቶ ሓሰን ዑመር መልዕክት የዝምታና የፍራቻ  የፖለቲካ ባህላችንን መቀየር በአገራችን እንዲመሰረት ለምንመኘው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል። ስለሆነም በቅርቡ በአንዳንድ የግሉ ፕሬስ ውጤቶች በሆኑ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ የምናነባቸውን በተቃዎሚ መሪዎችና ድርጅቶች ላይ በግልጽ የሚሰነዘሩ ገንቢ የሆኑ ትችቶችን እንደ አንድ እርምጃ ወደፊት ልናያቸው ይገባል። ቻይናዎች የአንድ ሺህ ማይል ርቀት ያለው ጉዞ በአንድ እርምጃ ይጀመራል የሚል አባባል አላቸው።

## ማጠቃለያ

የአንድ አገር ሕዝብ በሙሉ በፖለቲካ ሊሳተፍ አይችልም። የፖለቲካ ጫወታውን የሚጫወቱት ፖለቲካኞችና ፓርቲዎቻቸው ናቸው። ሆኖም ግን ሕዝብ በአገሩ የዴሞክራሲያዊ ግንባታ የሚጫወተው ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ዴሞክራሲም የሕዝብ አስተዳደር ማለት ነው። ዴሞክራሲ ሊሰራ የሚችለው ደግሞ በውክልና ነው። ውክልና ደግሞ የስልጣን ባለቤት ከሆነው ሕዝብ ለፖለቲካ ፓቲዎችና መሪዎቻቸውና ግለሰቦች ለተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ ሥልጣን ነው። ስለሆነም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የፖለቲካ አቅጣጫውን የመቆጣጠር ኃላፊነት የሚወድቀው በሕዝብ ተውካዮች ላይ ቢሆንም ዋነኛው ኃላፊነት ግን ያለው በራሱ በመራጩ ሕዝብ ላይ ነው። ሕዝቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያቀርቡለትን አማራጮች በሚጋባ መርምሮ ለሚፋልገው ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው ያለውን እምነት በምርጫ ድምፁ በመጠቀም መሪዎቹን መርጦ ለስልጣን ያበቃቸዋል።ውክልና ከመስጠታችን በፊት ግን የምንወልለውን ድርጅትና መሪውን ማንነት በሚገባ ጠንቅቀን ማወቅ ይገባነል። ውክልናን ከእምነት ጋር ለይተን ማየት አንችልም። ስለሆነም የዛሬውን የተቃዋሚ እና የነገውን የአገራችን መሪዎችን ዛሬ በሚገባ ልናውቃቸው ይገባል።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጥሩ ወይም መጥፎ ሰው ናቸው በሚል የራሴን ፍርድ የመስጠት መብትም ሆነ ፍላጎት የለኝም። ሆኖም ግን ኮሎኔሉ የሚያራምዱት ፈጽሞ ግልጽነት የጎደለው ፖለቲካ ከወያኔ አገዛዝ ጋር የሚደረገውን ትግል ይጎዳል ብዬ የራሴን ግንዛቤ እየተነተኑ የማቅረብ መብት ግን ማንም ሊሰጠኝና ሊነፍገኝ የማይችለው የዜግነት መብት እንደሆነ አጠያያቂ አይደለም። በኮ/ል ጎሹ ወልዴ ላይ የሚታየው የአቋምና የእምነት መለዋወጥ ምክንያቱን ይህ ነው ብዬ መናገር አልችልም። ዛሬ ኮሎኔሉ ለሕዝቡ የጦርነት መንገድ አያዋጣም፣ ኤርትራ አንዴ ተገንጥላ እውቅና ያገኘች ነፃ አገር ሆናለችና የምን ሙጥኝ ማለት ነው ባይሆን ይቅናችሁ ብሎ መሰናበት እንጂ፣ የተቃዋሚ ኃይሎችን ህብረት ግንባር የኢ.ሕ.አ.ፓ ስብስብ እያሉ ማጥላላትና በሌላ በኩል ትላንት በወያኔ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ላይ ያሰሙት የነበረው ጠንካራ የተቃውሞ ድምፅ ቀንሶ ከዜሮ በታች በሚገኝበት በአሁኑ ሰዓት ላይ ትናንት ሲያካሂዱት የነበረውን ፖለቲካ ለምን እንደቀየሩ እየተነተኑ ሕዝቡን በማስረዳትና በማሳመን ፈንታ ራስን ሰላም ወዳድ አድርጎ በማቅረብ ሌላውን በጦረኝነት መክሰስና ይህንንም እንደ ታክቲክ ተጠቅሞ በመድኅን ላይ አንጃ መፍጠርና የውህደት ፖለቲካን በመስበክ ህብረትን በማንቋሸሽ የሚካሄድ ፖለቲካ ለትግሉ ፈጽም ጠቃሚ አይደለም።

አቶ መሓመድ አህመድ ጋስ ትላንት ይወክሉት የነበረውን ድርጅታቸውን አርዱፍንና የአፋር ሕዝብን ትግል በመክዳት በድርጅታቸው ላይ ተለጣፊ አርዱፍ ፈጥረው ራሳቸውን የአንጃው ሊቀመንበር አድርገው በመሾም የወያኔን አገዛዝ ሥርዓት እውቅና አግኝተው ለሰሩት ውለታ የሞቀ ወንበር ከተሰጣቸው ጥቂት ወራት ሆኗቸዋል። የዛሬውን አያድርገውና ትናንት ወያኔና ሻዕቢያ ጦርነት ላይ በነበሩብት ሰዓት ላይ አቶ መሓመድ አህመድ ጋስ በአንድ ስብሰባ ላይ በንግግራቸው ላይ አርዱፍ የተናጥል የተኩስ አቁም ስምምነት ማድረጉን ይገልፃሉ። አንድ የስብሰባው ተሳታፊ በንዴት እሳት ጎርሶ ለምን ብሎ ይጠይቃል፡፤ አቶ መሓመድ ጋአስ ሲመልሱ፣" …ጠላታችን ወያኔ ጠላታቸ ሻዕቢያን ለመውጋት ሲሄድ አታሳልፉ እንዴት ይባላል ? ባይሆን ወያኔ ሲመለስ መንገድ ይዘጋበት በሉ እንጂ…"በማለት ለቀረበላቸው መልስ ሰጥተው ነበር። ይህው ዛሬ አቶ መሓመድ አህመድ በጠላታቸው ወያኔ የወጣቶች ስፖርትና ባህል ምክትል ሚኒስትር ሆነው በመሾም የተደላደለ ኑሮአቸውን ተያይዘውታል። ሌላውም ነገ ተራውን እየጠበቀ ወይ አማካሪ ካልሆነም ፕሬዚዳንት እየተባለ ቢሾም የእኛም ጥፋት እንዳለበት በመጠኑም ቢሆን ልንገነዘብ ይገባል።

በመኢአድና በኢዴአፓ መሃከል ተሞክሮ ለከሸፈው ውህደት ጥፋተኛው ክቡር አቶ ኃይሉ ሻውል መሆናቸውን ለማወቅ የግድ የፖለቲካ ፈላስፋ መሆንን አይጠይቅም። ይህም የሕዝብን ድጋፍ በመበተን በትግሉ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጥፋተኛውን ያለ ምንም ይሉኝታ መተቸት ተገቢ ነው። በአገዛዙና በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች መካከል የተፈጠረውን ግጭት አስመልክቶ የኢዴአፓ ም/ሊቀመንበር ክቡር ዶ/ር ሃይሉ አርአያ የተናገሩት ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ይህ የግል አመለካከት ወይስ የድርጅት እምነት፣ የግል አመለካከት ከሆነ ድርጅታቸው እንዴት ሊያስተበብል እንዳልሞከረ በመተቸት በምናገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጠይቀን ለመረዳት መሞከር ይገባነል፡፤

በሕዝቡና በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የሰለጠነ ግንኙነት እንዲኖር ያስፈልጋል። ለሕዝብ ትችት ራሱን ማስገዛት ከማይችል ፖለቲከኛ ብዙም መጠበቅ አይኖርብንም። እንደ ሕዝብ በእኛ ስም ለሚካሄድ ፖለቲካ የመደገፈና የመቃወም መብታችንን በመጠቀም ከሕሊናችን ጋር የመራመድ መብታችንን የምንወስነው እኛው እራሳችን መሆናችንን መገንዘብ ይኖርብናል። ይህን መብታችንን በመጠቀም መደገፍ ብቻ ሳይሆን የሚያራምደው ፖለቲካ ከእኛ ፍላጎትና ጥቅም ጋር አብሮ የማይሄድ ሆኖ ስንገኘው ድጋፍ በመንፈግ የማግለሉንም ባህል መልመድ ይኖርብናል። የወያኔ አገዛዝ ሕዝብ የሚወዳቸን ፖልቲከኞች ከሕዝቡ ጉያ እየነጠቀ የተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞባቸው በሕዝብ ዘንድ እንዲጠሉ አድርጎ ሲጥላቸው ተመልክተናል። ይህ መሰሪ ፖለቲካ እንዲያበቃ ማድረግ ይኖርብናል። የተቃዋሚ መሪዎችም እያፈነገጡ በወያኔ አገዛዝ ረድፍ ውስጥ መግባት ትግሉን እጅግ በጣም ሊያዳክመው እንድሚችል ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል።ሕዝብ የጣለውን ፖለቲከኛ ወያኔ አያነሳውም። የወያኔ አገዛዝ እንደ አቶ መሓመድ አህመድ ጋስ ሊያደርጋቸው የሚፈልጋቸውን የወደፊት እጩ የተቃዋሚ ፖለቲከኞችን አስቀድመን በመለየትና በማግለል በሥርዓቱ ዘንድ የሚኖራቸውን ተፈላጊነት ከዜሮ በታች በማድረግ ትግሉን በንቃት በመጠበቅ እኛም እንደ ሕዝብ የሚጥበቅብንን በማድረግ ትግሉ እንዲጠናከርና የምንመኘው የዲሞክራሲ ሥርዓት እንዲመሰረት የበኩላችንን ማድረግ ይኖርብናል። ትናንት ሙዚቃንና ፖለቲካን ስናወዳድር ሙዚቃን የምናውቀው ከሙዚቃኞች ሲመጣ ነበር። ዛሬ ግን ትንሽም ቢሆን ኖታ ማንበብ ጀምረናል። በየቤቱና በትናንሽ ጠረጴዛዎች ዙሪያ ላይ ከወዳጆቻችን ጋር ስለ አንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው የምናደርጋቸው ውይይቶች አሁንም ቢሆን በአብዛኛው የሚሰጡን ትምህርት ግንዛቤን ለመፍጠር እንጂ የባህርይ ለውጥ ለማምጣትና እርምጃ ለመውሰድ እምብዛም ያልጠቀሙን መሆናቸውን ነው። ስለሆነም ይሉኝታችንንና ዝምታችንን እየሰበርን ድምፃችንን ከፍ እያደረግን በማሰማት የምንፈልገውንና የማንፈልገውን ፖለቲካ ለይተን የምናውቅ መሆናችንን ለተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና ለሚመሩት ድርጅት በማሰማት በብልጣ ብልጥ ፖለቲካ የምንታለልበት ጊዜ ማለፉን ማሳወቅ ይኖርብናል። ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም አማራጭ የለንም።